## ግልጽ ደብዳቤ፡ ለስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት “የመድረክ” መስራቾችና “የአንድነት” ፓርቲ የ”ክብር” እንግዶች

### ምጥማጥና ዶሮ አንድ ላይ ሰፈሩ
### ቢቸግር ነው እንጂ መች ጓዶች ነበሩ

የዚህ አጭር ጽሁፍ አላማ በቅርቡ በተቋቋመው “የምክክር መድረክ” በተባለው ግለሰቦችን፤ ፓሪቲዎችን፣ ቡድኖችን አሰባስቦ በያዘው የወንጀለኞች ጥርቅም የተወሰኑ የአመራር አባላት ላይ ያነጣጠረ ይሆናል።

እንደሚታወቀው በወያኔ ውስጥ ከተራ አባልነት እስከ የመከላከያ ሚ/ር ማዕረግና የክልል ፕሬዚዳንትነት የስልጣን እርከን የተቆናጠጡት ስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት ከቅርብ ግዜ ወዲህ “በምክክር መድረክ” ለኢትዮጵያ መስራች በመሆን እንዲሁም “በአንድነት ፓርቲ” ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የበላይ ጠባቂነት ካባ በማጥለቅ ለኢትዮጵያ ህዝብ አዲስ ራዕይ እንዳነገቡ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በሰጧቸው ቃለምልልስ፤ ጋዜጣዊ መግለጫዎችና ፎቶ ሪፖርቶች እራሳቸውን ለማስተዋወቅ ጥረት አድርገዋል። ነገር ግን፦

1. ስዬ አብርሃና ገብሩ አስራት ከደርግ ጋር በነበሩት ከፍተኛ ፍልሚያዎች ወቅት በተለያየ ዘርፍ የወያኔን ሰራዊት በመምራት ለድል ካበቁት መሪዎች ተጠቃሾቹ ሲሆኑ በወቅቱ ከሻዕቢያ ጋር የነበራቸውን ግንኙነትና አንድነት በዝርዝር እስከዛሬ ትንፍሽ ብለው አያውቁም! ለምን?
2. ሻዕቢያን ከመጨረሻ ግብአተ መሬቱ ለማዳን በናቅፋ ተራሮች ላይ በተደረገው ወሳኝ ፍልሚያ ከትግራይ ተመልምለው መስዋዕትነት ስለከፈሉት የጎውሃት ታጋዮች ዝርዝር መረጃ ለምን ይፋ አላደረጉም?
3. በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ ሰራዊት ከመጨረሻ ግቡ እንዳይደርስ በመለስ ዜናዊ ስለተላለፈው የማፈግፈግ ትእዛዝ ይህንን ተከትሎ ሰለደረሰው ሽንፈትና ውድመት ለምን ዝምታን መረጡ?
4. በምስራቅ ኢትዮጵያ ለከት በሌለው አፋቸው እኛ ጦርነት መስራት እንችላለን በማለት በተቀረው ህብረተሰብ ላይ ያላቸውን ጥላቻና ንቀት በግልጽ በአደባባይ ለተናገሩት የጀብደኝነት ቃላት ህዝቡን ለምን ይቅርታ አልጠየቁም?
5. ሻዕቢያዎች በአ. አ. ከተማ ውስጥ የተለያዩ የአፈናና የግድያ ተቋሞችን ዘርግተው ኢትዮጵያን በቅኝ በሚያስተዳድሩበት ወቅት ያደረሱትን ጥፋቶች ማለትም በአስተዳደር፤ በገንዘብ፤ በሞራል …. እስከ ዛሬ ምነው ትንፍሽ አላሉም?
6. ከነበራችሁበት የመንግስት ስልጣን በመነጨ ሻዕቢያ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ተቋሞች በመቆጣጠር ኤርትራ በአለም 18ኛዋ የቡና ላኪ ሀገር ስትሆንና ከኢትዮጵያ ባንኮች ኤርትራውያን በቀበሌ መታወቂያ ደብተር ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ ያለምንም መያዣ በብድር መልክ ሲቀራመቱ፣ እንዲሁም የወርቅ፤ የአጣና፤ የሌጦ ወዘተ ኤክስፖርቶችን ያለምንም ተቀናቃኝ በባለሃብትነት ሲያጋብሱ፤ በተጨማሪ ከፍተኛ የኢትዮጵያን የልማትና የንግድ ተቋሞችን እንዲሁም መንግስታዊ ድርጅቶችን በእናንተ (ወያኔ) ፈቃድ በኤርትራያውያን እጅ ሲወድቁ ለምን ዝምታን መረጣችሁ?
7. የኤፈርት የንግድ ተቋሞችን በተመለከተ ግልጽ አቋማችሁ ለምን አላስቀመጣችሁም?
8. ገብሩ አስራት ከዚህ ቀደም ለትግራይ ክልል የግል ጋዜጣ አያስፈልጋትም ብለው ማገዳቸውን ለምን እንደሆነ ለምን አላብራሩልንም?
9. በሀኒሽ ደሴቶች ውግያ ወያኔ ለሻዕቢያ ስለሰጠው የአየር መቃወሚያና የራዳር ባትሪ አጠቃላይ መረጃ ለምን ዝምታን መረጡ?
10. በ1991 የመጀመሪያዎቹ አመታት ወደ ኤርትራ ስለተጓጓዘውና በኢትዮጵያ ስም ሻዕቢያ ተበድሮ ስላልመለሰው ከፍተኛ መጠን ያለው የብድር ገንዘብ በተመለከተ ለህዝብ ትክክለኛውን መረጃ ለምን አላቀረቡም?
11. ከጎንደርና ከወሎ ተወስደው ወደ ትግራይ ስለተካለሉት ቦታዎች አቋማቸው ምን እንደሆነ ለመናገር ምነው ተንሸራተቱ?
12. በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ሰለተመለሱትና ወደቀድሞ ስራ ቦታቸው (back payment) ሁሉ እየተከፈላቸው ስለተመደቡትና፤ እንዲሁም የቀድሞ ንግዳቸው እየተመለሰላቸው ስላሉት በጦርነቱ ወቅት የተባረሩ በሺዎች የሚቆጠሩ የኤርትራ ዜጎች ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ለምን ዝምታን መረጡ?
13. ጥቂት የትግራይ ተወላጆች በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ የአገሪቱን ኢኮኖሚ፡ በብቸኝነት የተቆጣጠሩ ሲሆን የሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች በድህነት እየማቀቁ ይገኛሉ በተጨማሪ ሁሉም

*የመንግስት የስራ ተቋማት ከአንድ ክልል በመጡ ተወላጆች መሞላት በማስመልከት የወያኔን ፖሊሲ ሲቃወሙ ምነው አልተሰሙ?*
*14. ወ/ሮ አዳነች ኪዳነ/ማርያም በአንድ ወቅት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በነበራችበት ወቅት ከኢትዮጵያ መንግስት ካዝና ለህውሃት ለመድሃኒት መግዣ ከመንግስት ካዝና ስለተመዘበራውነ ስለተከፈለው የህዝብ አንጡራ ሃብት ለምን ማብራሪያ አጠራቸው?*
*15. በቅርቡ ወደ ሱዳን ስለተካለሉት የምዕራብ ኢትዮጵያ አዋሳኝ መንደሮችና ቦታዎች ግልጽ አቋማቸውን ለምን በድፍረት አላስቀመጡም?*

*እነዚህንና ሌሎች መሰል እስከዛሬ ምላሽ ያላገኙ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥያቄዎች እናንተ በአገዛዙ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ በነበራችሁ ግዜ የተፈጠሩና የተከናወኑ ድርጊቶች ግልጽና ግልጽ በሆነ መንገድ እውነታውን ሳታሳውቁ በተድበሰበሰ መንገድ አሁንም "የምክክር መድረክ" ከተባለው የወያኔ ቅጅ የጎሳ ድርጅት ጋር ተዋህዳችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ እንታገላለን ማለት የበደልናችሁን እርሱትና ዛሬም እንደትላንቱ ላያችሁ ላይ ተጭነን እንግዛችሁ በማለት አይናችሁን በጨው አጥባችሁ ያለአንዳች እፍረት መቅረባችሁን ያመለክታል።*

*"መድረኩ" እንደዚህ ከመሰሉ የህዝብና የሃገር ጠላቶች ጋር ተሞዳምዶ ለመስራት መወሰኑ ለስልጣን እንጂ ለህዝብ ደንታ እንደሌለው ያስረዳል። ለነገሩ "በመድረኩ" ውስጥ የተካተቱት በሙሉ በህውሃት መንግሰት ውስጥ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ያገለገሉ አሁንም እያገለገሉ ያሉ የስልጣን ቋማጮችና ጠባብ የጎሳ መሪዎች ስብስብ መሆኑ ያፈጠጠ ሀቅ ነው።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!*

*ሙኒር ነጋሽ*